ይድረስ፦

በቅዱሱ ኪዳን፡ ወንድሜና የክህነት ባልደረባዬ ለኾንከው፡ የተወደድክ ኪዳናዊ ዮሓንስ ደጉ!

በመንፈስ-ቅዱሳዊው ዕውቀትህ፡ "መንፈስ፣ መንፈስ-ቅዱስ፣ መንፈስ-ርኩስ" በሚል ርእስ ላቀረብኸው ምርምር፡ እኔም በበኩሌ፡ በዚያው መንፈስ-ቅዱሳዊው ዕውቀቴ፡ ለሰጠሁህ የማሟያ መልሴ፡ ሌላ ተጨማሪ ቀጣይ ምርምር አካኺደህና በጽሑፍ አዘጋጅተህ፣ ያንኑም፡ በኹለቱ የቅጂ ቅጾች ከውነህ የላክህልኝን ድርሰት፡ በዐባሪነት የያዘው እ-ጦማርህ ደረሰኝ፤ እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

ይኸው እ-ጦማርህ፡ የአንተንና የኪዳናዊ ቤተሰብህን ደኅንነት፥ በ"ኪዳናዊው ደስታም ተጠብቃችሁ የምትገኙ" መኾናችሁን ስላበሠረኝ፡ እኔም ተደስቼ፣ በያለንበት የሚጠብቁንንና የሚመግቡንን፥ የሚመሩንንና በዕውቀታቸው የሚያሳድጉንን፡ ዘለዓለማውያኑን ቸር ወላጆቻችንን አመሰገንሁ።

የአኹኑም ጥልቅ የምርምር ጽሑፍህ፡ እንዳለፈው ኹሉ፡ በመንፈስ ቅዱስ የዕውቀት በረከት የተመላ በመኾኑ፡ የኹላችንንም የኢትዮጵያን ልጆች ኪዳናዊ የዕውቀት አድማስ የሚያሰፋ ኾኖ ስላገኘሁት፡ በጥልቅ እርካታ ተመልቼ፡ ይህን ጸጋ ላደለን እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስ፡ ምስጋናዬን አቀረብሁ፤ አንተንም፡ ከምርቃቱ ጋር አሞገስሁ።

በእግዚአብሔራችን ኢየሱስ መሢሕ ሰውነት ገዝፎ፡ አያሌ መለኮታውያን ምስጢራትን የገለጠልን፡ ይኸው መምህራችን እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስ፡ ወንድማችንን ኪዳናዊ ሓኪም ዘርፉ መልአኩን መነሻ አድርጎ፡ በዚህ ረገድ፡ የከፈተውን የዕውቀት ገበታ፡ በበለጠ ሊያሟላው ስለፈለገ፡ ይኸው፡ በአንተ እና በእኔ መሣሪያዎቹ አማካይነት፡ ይህ የጽሑፍ ልውውጥ፡ በመካከላችን እየቀጠለ እንዲካኼድ ፈቃዱ ኾኖ፡ ቸርነቱን ሲያበዛልን፡ እነሆ እንመለከታለን።

በዚህ እውነታ መሠረት፡ የአኹኑን የምርምር ዝግጅትህን፡ ፍጹም ለማድረግ፡ በእኔ በኩል፡ ከዚህ የሚከተሉት፡ አንዳንድ፡ የማብራሪያና የማሟያ አሳቦች እንዲታከሉ፡ በዚያው በመንፈስ ቅዱስ መርሕ አቅርቤያቸዋለሁ፦

ከዚያ በፊት ግን፡ በቀደመው የመልስ ጽሑፌ ውስጥ፡ በምሳሌነት፥ ወይም፡ በበለጠ ማብራሪያነት፡ "ለማስረጃ ያህል" ብዬ ያቀረብኋቸውን፡ አንዳንድ ቍም-ነገሮችን በሚመለከት፡ ልገልጽልህ የሚያስፈልገኝ ማስገንዘቢያ አለኝ፤ ይኸውም፡ ምናልባት፡ አገላለጼና አቀራረቤ፡ ያን እውነታ ለማንጸባረቅ ሳይችል በመቅረቱ ይኾናል እንጂ፡ እነዚያ ቍም-ነገሮች፡ የአንተን ኪዳናዊ የሃይማኖት አቋም፥ ወይም፡ ቅን የኾነውን የምርምርህን ትክክለኛ አግባጫ፡ በምንም መልኩ ለአጠያያቂነት በመዳረግ፥ ወይም፡ ምርምርህ፡ እንከን ኖሮበት፡ ያን ለማጥዳት፥ ወይም፡ ለማቃናት ታስቦም እንኳ፡ የቀረቡ እንዳልኾኑ፡ በቅድሚያ የማረጋግጥልህ እውነታ ነው።

"'፩+፩+፩=?' ተብሎ፡ ከአንድ እስላማዊ አማኝ ለቀረበው ጥያቄ፡ የሰጠሁትን መልስ የመሰሉትን" ማለቴ ነው። እንዲሁም፡ 'ነፈሰ' በሚለው ቃል መነሻነት፡ እኔ በማብራሪያ መልሴ ውስጥ የሠነዘርሁትና አንተም፡ በአኹኑ ምርምርህ የጠቀስኸው ትችቴ፡ *"እኔ የኼድኩበትን ላካኼድ የሚገልጽ ኾኖ ላላገኘሁትም።"* ብለህ ለደመደምኸው የመልስ ቃልህ፡ ይህንኑ ቃልህን ባሠፈርህበት ዐቢይ ዐረፍተ-ነገር ውስጥ፡ ቀደም ብለህ፡ *"ስለዚህም ስለእግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስ ማንነትና ምንነት፡ እንደማስረጃ ኾነው መቅረባቸው፡ "ግንዛቤ እንዲጨምር ያደርጋሉ።" የሚል እምነት ላለኝ።"* ያልኸው ሌላው ቃልህ፡ በዚሁ፡ በእኔ ትች መኻል፡ **"አንዱ ስለሌላው ምንነትና ማንነት ለማብራራትና ለማስረጃነት ያህል፡ የሚጠቃቀሱ፣'** ከሚለው ጋር፡ ፍጹም የተስማማ ኾኖ የመገኘቱን እውነታ!" ማለቴ ነው።

በአጠቃላይ፡ የእኔ አቀራረብ ዋና ዓላማ፡ ሌላው አላዋቂ፥ ወይም፡ የክፉው ዝንባሌ ሰለባ የኾነው አንባቢ፡ ያንን፡ አንተ፡ በእውነት መንፈስ ያቀረብህበትን ዕውቀት፡ ምናልባት፡ በቅኑ ኅሊናው ሳይኾን፣ የዚያ ተቃራኒ በኾነው፡ በክፉው አስተሳሰብ ከመውሰዱ የተነሣ፡ ባለማወቅ፥ ወይም፡ በትክክል ባለመረዳት፡ ወደማይፈለገውና ወደተሳሳተው አግጣጫ እንዳይኼድ፡ በዚህ ኣጋጣሚ፡ በበለጠ በማስረዳትና በማብራራት፡ ከአላዋቂነት ጥፋቱ ለማዳን፣ ለሌሎች አላዋቂዎችም፡ ትምህርት እንዲኾናቸው ነው።

በዚህ ረገድ፡ ብዙውን ጊዜ፥ ወይም፡ አንዳንድ ጊዜ እየደረሰ የሚታየው፣ እየኾነም ያለው እውነታ፡ በአንዱ ሰው፡ የቀረበውን አሳብ፣ ወይም፡ የተሠነዘረውን ትች፡ ሌላው ተቀባዩ ሰው፡ ያን አሳብ፥ ወይም፡ ትች፡ ሰምቶ፥ ወይም ተመልክቶ የሚያስተናግድበት፣ ማለትም፡ የሚያመዛዝንበትና የሚገመግምበት፥ የሚያነጻጽርበትም መንፈስ፡ አንድ ዓይነት ሳይኾን ይቀር፣ ወይም፡ የተለያየ ኾኖ ይገኝ ይኾናል። ይህን የመሰለው ኹኔታ በሚደርስበት ጊዜ፡ በሌሎች ዘንድ፡ አለመግባባትን የሚፈጥር ቢኾንም፡ ለእኛ፡ ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ግን፡ ምንም ዓይነት ችግርን የሚያነሣሣብን አይኾንም፣ ምክንያቱም፡ በዚያ በተቀባዩ ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘው፡ ማናቸውም ዓይነት አስተሳሰብ፡ ለዚያ ሰው፡ "በመንፈስ ቅዱስ የተገለጸ እውነታ ነው!" በሚል መልክና ይዘት፡ አቅራቢውም ኾነ፡ ተቀባዩ፡ ኹለቱም ወገኖች፣ በቅንነት መንፈስ ስለሚያስተናግዱት ነው።

በቅድሚያ ልገልጸው ስለፈለግሁት ማስገንዘቢያ፡ ይህን ካልሁ፡ አኹን ደግሞ፡ በአንተ፡ በኪዳናዊው ወንድሜና የክህነት ባልደረባዬ በኩል፡ በዚህኛው በቀጠለው የምርምር ጥናትህ ዝግጅትና አቅርቦትህ ረገድ የተገለጸው ኹሉ እንዳለ ኾኖ፡ በአጽንዖት ላጠናከረው በመፈለግ፡ የምጨምረው ቊም-ነገር ቢኖር፡ በዚህም ረገድ፡ በእኔ በኩል ደግሞ ያለውን፡ የመንፈስ ቅዱስን ዕውቀት ማበርከት ይኾናል። ለዚህ የተልእኮ ድርሻዬም፡ መነሻ የማደርገው፡ እንዲህ የሚለውን፡ ከአኹኑ፡ ከአንተው የምርምር ጽሑፍ፡ የተጠቀሰውን ቃል ይኾናል።

አዎን! *"በዚህ ተፈጥሯዊ ንቃት ውስጥ ኾኜ* [ማለትም፡ ዛሬ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኪዳናዊ ልጅነቴ፣ ነጋሢነቴና ክህነቴ] *ሳየው፡ ስለመንፈስ የአካል ምንነትና ማንነት፡ ግር እንዲለኝ ያደርግ የነበረው፡* ***"ረቂቅ አካላት ኹሉ አንድ ዓይነት የአካላት ባሕርይ ያላቸው ኢድርን መገንዘቡ ነው"*** *ወደሚል ግንዛቤ ደርሻለሁ፤ ማለትም እግዚአብሔር አብወእም፣ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስ አንድ ዓይነት ባሕርይ ያላቸው አካላት ኢድርን መገንዘቡ ነው፤ ወይም የየአካላቱ የባሕርይ ልዩነት ምን ማለት እንደኾነ፡ በትክክለኛው ኹኔታ አለመረዳቴ ነበር። ስለዚህም፡ የሦስቱንም አካላት ማንነትና ምንነት ለመገንዘብ ጥረት ማድረግ እንዳለብኝ ተገንዝቤያለሁ።"* የሚለውንና አንተም፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ተገቢውን የመፍትሔ ምላሽ ያብራራህበትን ኃይለ-ቃልህን ይኾናል።

ይህም የእኔ የተልእኮ ድርሻ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን ዕውቀት የሚያሳድግ፣ ተጨማሪ ማብራሪያንም፡ ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ ላወቁት፡ የዕውቀታቸው ማጠናከሪያ፥ ለተሳሳቱትም፡ ከስሕተታቸው መመለሻ፥ ላላወቁትም፡ የአላዋቂነታው ማስወገጃና ማሳወቂያ እንደሚኾናቸው አምናለሁ።

እንግዴህ፡ የዕውቀቱ ማብራሪያ እንዲህ ይላል፡- እግዚአብሔር፡ አንድ ነው። በባሕርዩም፡ አንድ ነው። እንዲህ፡ በባሕርይ፣ ማለትም፡ በፈጣሪነት፣ በእግዚአብሔርነት፣ በመለኮትነትና በአምላክነት፡ አንድ ሲኾን፡ ስለፈጠረው ፍጥረቱ፣ በተለይም፡ በመልኩ ፈጥሮና **"ኮነ፡ ከመ አሐዱ እምኔነ!** ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ብሎ፡ ከራሱ ጋር ስላስተካከለው ስለሰው ሲል፡ ፈጣሪ፡ አንድ ራሱን፡ "እግዚአብሔር አብወእም"፣ "እግዚአብሔር ወልድ" እና "እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስ" በሚሉ፡ ሦስት አካሎች፣ በሦስት ስሞችና በሦስት ግብሮች መድቦ፡ በባሕርይ አንድነት እና በስም፣ በአካልና በግብር ሦስትነት ህልውና፡ በሕያውነት እየሠራ ይኖራል።

የባሕርይ አንድነቱን፡ "እግዚአብሔር" በሚለው አጠራሩ፡ ያረጋገጠ ሲኾን፡ የስም፣ የአካልና የግብር ሦስትነቱን ደግሞ፡ "አብወእም"፣ "ወልድ"፣ "መንፈስ-ቅዱስ" በሚሉት አካሎቹ እና ስሞቹ፣ እንዲሁም፡ ግብሮቹን፡ በልጅ፡ ወላጅነቱና በመንፈስ፡ አሥራጺነቱ፣ በተወላጅነቱና በልጅነቱ፣ በሠራጺነቱና በሕይወትነቱ አረጋግጧል። "ምስጢረ-ሥላሴ" የሚባለውም፡ ይህ ነው።

በማስተዋል ለሚመለከት ኹሉ፡ ይህ፡ የፈጣሪ፡ በአንድነትና በሦስትነት የመገለጡ ምስጢርና እውነታ፡ እውን ኾኖ፡ ተፈጻሚነትን ያገኘው፡ ይኸው፡ "እግዚአብሔር" የምንለው፡ ፈጣሪ፡ ለራሱ፡ ሊከብርበትና ክብሩን ሊጨምርበት፣ ሊመሰገንበትና ገናንነቱንም ሊያልቅበት አለመኾኑን፡ በማረጋገጥ ሊመሰክር ይቻለዋል።

ነገር ግን፡ ይህ፡ የፈጣሪ፡ በአንድነትና በሦስትነት የመገለጡ ምስጢርና እውነታ፡ እውን ኾኖ፡ ተፈጻሚነትን ያገኘው፡ ለፍጥረቱ፣ በተለይም፡ ምንም ችግር ሳይኖርበት፡ ራሱ ተቸግሮ፣ በይበልጥ፡ ፈጣሪውንም እያስቸገረ ላለው፡ ለሰብአዊው ፍጡሩ፣ ከዚያም ዐልፎ ተርፎ፡ "ሰይጣን" ለተባለው፡ ዓመፀኛ ፍጡሩ እንኳ ሳይቀር፣ ለኹሉም ተነሳሒነት [ወደበጎው፡ በንስሓ መመለስ]፤ መልካምነትና ደኅንነት፥ ሰላምና ደስታ ሲል መኾኑ፡ በሥነ-ፍጥረት ህልውናና ኺደት፡ እነሆ፡ በገሃድና በግዘፍ፡ ያለማቋረጥ እየታየ ነው።

ይህን እውነታ፡ አንተም፡ በምርምር ጽሑፎችህ ውስጥ፡ ጥሩ አድርገህ፣ አስፋፍተህና አሟልተህ አቅርበኸዋል፤ አኹንም፡ "ነገርን፡ ነገር ያነሣዋል!" ነውና፡ እስኪ፣ እኔም፡ ይህንኑ ዓቢይ ቍም-ነገር፡ በበለጠ ላብራራው ብዬ፡ እዚህ ላይ፡ እንዲህ እያልሁ አክዬበታለሁና፡ ተመልከተው፡-

ከላይ በሠፈረው የእውነት ቃል መሠረት፡ እግዚአብሔር፡ በዚህ ማንነቱ፡ የእየአንዳንዳችን፡ የኹለንተና ሰውነት ፈጣሪ፣ እንዲያውም፡ ራሱ፡ እየራሳችን መኾኑ ብቻ ሳይኾን፡ አባታችንና እናታችን፥ እኅታችንና ወንድማችን፥ ጓደኛችንም ኾኗል። በነፍሳዊው እና በመንፈሳዊው ርእዮትና ዓለም ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በሥጋዊው ምርምር ጭምር ለማረጋገጥ፡ በቁርጥ ፈልጎ ለተነሣ፡ ለማንም ሰው፡ በአሳብም ኾነ፡ በግዘፍ፡ ወደሩቅ መኼድ፥ ወይም፡ ወደላይ መምጠቅ፥ ወይም፡ ወደታች መጥለቅ፣ ወይም፡ ዙሪያውን በማንገዋበብ፡ መራቀቅ፥ ወይም፡ አካባቢን በመቃኘት፡ መጠበብ አያስፈልገውም። በእውነት ካስተዋለው፡ እዚሁ፡ በቅርቡ፡ በእየአፍታው፡ በእየራሱ እየኾነና እያደረገው ባለው፡ ሊያውቀውና ተረድቶ ሊቀበለው፣ ሊያምነውም ይቻለዋል።

ይኸውም፡ የዚህን ታላቅ ቍም-ነገር እውነታ ለማረጋገጥ፡ በቁርጥ ፈልጎ የተነሣው፡ ያ ማንኛውም ሰው፡ እውነተኛውን የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትን ተቀብሎና በዚያ ጸንቶ የሚኖር፣ በዚሁ ሃይማኖቱም፡ ከብቅዓቱ የደረሰ ከኾነ፡

፩. በእግዚአብሔር መልክ እና "ከእኛ እንደአንዳችን ኾነ!" ተብሎ፡ የተፈጠረበት፡ ሥጋዊው፥ ነፍሳዊውና መንፈሳዊው ሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር፣ በእግዚአብሔር እና ለእግዚአብሔር መኾኑን፣ ከዚህ የተነሣም፡ ገና በማሕፀን ሲፀነስ፡ ነፍሱ፡ ከእግዚአብሔር አብወእም፥ ሥጋው፡ ከእግዚአብሔር ወልድ፥ መንፈሱም፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተከፍለው የተገኙና በተዋሕዶ የከበሩ መኾናቸውን፣ ስለዚህም፡ በሰውነቱ፡ እንደፈጣሪው፡ በአካል፥ በስምና በግብር፡ እንዲህ፡ ሦስትነት ያለው፣ ባሕርዩም፡ አንድነት ያለው መኾኑን ይገነዘባል።

፪. ይህ፡ ዕፁብ-ድንቅ የተፈጥሮ አሠራር ሲተነተን፡ ይኸው ማንኛውም ሰው፡ ማኅየዊን [በሕይወት የሚያኖር]፥ መጽንዒን [ጽናትን=ጤንነትን የሚያድል] እና መንጽሒን [ኹለንተናን፡ ንጹሕ የሚያደርግ]፡ እኒህን ሦስት ባሕርያትን የተጎናጸፈውን፣ **እግዚአብሔራዊ መንፈስ፣** ደግሞም፡ የነባቢነትን [የመናገርን]፣ የለባዊነትን [የማስተዋልን] እና የሕያውነትን [ለዘለዓለም የመኖርን]፡ እኒህን ሦስት ባሕርያትን የተቀዳጀችውን፡ **እግዚአብሔራዊት ነፍስ፣** እንደዚሁ ኹሉ፡ ነፋስን፣ ፀሓይን [እሳትን]፣ ውኃንና መሬትን፡ እኒህን አራት ባሕርያትን ያዋሓደውን፡ **እግዚአብሔራዊ ሥጋ፡** ከፈጣሪው የወረሰ መኾኑን ይገነዘባል።

፫. እንዲህ፡ በምሉዕ-ከሃሊነት [ኹሉን ቻይነት]፡ ራሱን፡ እንደፈለገ ለማድረግ፣ ማለትም፡ በመልካሙ በመጽናት፡ እንደፈጣሪው ለመኾን፣ ወይም፡ ክፉውን በመከተል፡ የእርሱ ተፃራሪ ለመኾን እንዲችል፡ በፈጣሪው ታላቅ ቸርነት፡ ፍጹም የማሰብ ነጻነትና የመምረጥ መብት፣ የመወሰን ሥልጣንና የመፈጸም ኃይል የተሰጠው መኾኑን ይገነዘባል።

፬. በዚህ ጊዜና በዚህ ምክንያት፡ ይህ ሰው፡ በነፍሱ፡ የመንፈሱን፡ እግዚአብሔራዊ መመሪያና ምክር በመከተል፡ ራሱን፡ ማለትም፡ መላ ሰውነቱን፡ ለእግዚአብሔሩ የማንነትና የምንነት ማዕርግ ደረጃ ማብቃት የሚቻለው፣ የሚገባውም መኾኑን፣ አለዚያም፡ በዚያ፡ ፍጹም የማሰብ ነጻነቱና የመምረጥ መብቱ፣ የመወሰን ሥልጣኑና የመፈጸም ኃይሉ በመጠቀም፣ ምንም እንኳ፡ የማይገባውም ቢኾን፡ በክህደትና በዓመፀኛነት [በእምቢተኛነት]፣ ራሱን፡ ወደክፉነት ለመለወጥ የሚችል መኾኑን፡ በቀጥታ ይገነዘባል።

፭. የዚህን ኹሉ ምስጢርና እውነታ ለማብራራት ያህል፡ የሚታሰቡ ብቻ እንጂ፡ የማይታዩና የማይዳሰሱ የኾኑትን፡ የነፍስንና የመንፈስን ነገር፡ ለጊዜው ይተወውና፡ እስኪ፡ የግዙፉ ሥነ-ፍጥረት አካል የኾነውን፡ የሦስተኛውን **እግዚአብሔራዊ** የሰውነት፡ የሥጋ አራት ባሕርያትን ብቻ፡ በአብነትና በምሳሌነት ቢወስድ እንኳ፡ የሚያመርተው የእውነት ዕውቀት፡ ዕፁብ ድንቅ ይኾንበትና፡ በአንክሮና በተዘክሮ ሊመለከተው የሚወድድ መኾኑን ይገነዘባል። ይኸውም፡-

ሀ. በየቅጽበቱ፡ በአፍንጫው እየተነፈሰ፡ ባለው የእስትንፋሱ ነፋስ [በአየሩ]፡ ሕያው ኾኖ፡ ህልውናውን [ኑሮውን]፡ በሕያውነት እንዲቀጥል ያስቻለው ኃይል፡ በማኅየዊነቱ፡ ማለትም፡ በሕይወት ሰጪነቱ፡ ያ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መኾኑን ነው።

ለ. በፀሓይነቱ ደግሞ፡ ብርሃን ኾኖት፡ በዓይኖቹ የሚያየው፥ በሙቀቱ፡ የሰውነት ገላውን የሚያፈካው፣ በእሳትነቱም፡ ረቂቁን ኾነ ግዙፉን፣ አፍኣዊዉን ኾነ፡ ውሳጣዊዉን ተውሣክ አቃጥሎ፡ በላብነት ሳይቀር የሚያስወግድለት፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፡ እርሱ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር መኾኑን ነው።

ገ. በውኃነቱም፡ ይረካበት ዘንድ፡ የሚጠጣውና ሕይወቱን የሚያለመልምበት፣ አካላቱንም በመታጠብ የሚያጸዳበት፡ ያው እርሱው እግዚአብሔር መኾኑን ነው።

ደ. በመሬትነቱም፡ ምድር የምታበቅለውና በአበባነት አፍርታ፥ አበርክታና አብስላም የምትሰጠው፡ የአትክልቱ ቅጠላ-ቅጠልና የአዝርእቱ ጥራ-ጥሬ፥ የዛፉም ፍራ-ፍሬ፥ እንስሳቱ፣ አዕዋፋቱና የባሕር ዓሣዎቹ፣ ከእነዚህ ኹሉ የሚገኘው ተዋጽአው፡ ማሩና ወተቱ፣ ዘይቱና ቅብዓቱ፡ ሕይወትና ጉልበት እንዲኾነው፡ በምግብነት የሚጠቀምበት ሲሳይ ኹሉ፣ ከዚህም ጋር የሚረገጠው አፈሩና አሸዋው፣ ሣሩና ድንጋዩ፡ እርሱ፡ ራሱ እግዚአብሔር መኾኑን ይገነዘባል።

፯. ከዚህ የተነሣ፥ «"**ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ! እግዚአብሔር ጸባዖት! ፍጹም ምሉእ ሰማያተ ወምድረ።** ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ! አሸናፊ እግዚአብሔር! በሰማያትና በምድር፡ ፈጽሞ የመላ ነው።" በሚለው የምስጋና ቃል መሠረት፣ ደግሞም፡ እግዚአብሔር፡ ሙሴን፡- "**ፍታሕ አሣእኒከ እምእገሪከ! እስመ መካን፡ እንተ አንተ ትቀውም ባቲ ምድር፡ ቅድስት ይእቲ።** ጫማዎችህን፡ ከእግሮችህ አውልቅ! ይህች አንተ፡ የቆምህባት ምድር፡ ቅድስት ናትና።" ያለውን መለኮታዊ መመሪያ በመከተል፡ የሚራመድበት የመሬቱ ወለል ኹሉ፡ ራሱ እግዚአብሔር ስለኾነ፣ ኋላም፡ ይህን ቃል፡ ለሙሴ የተናገረ፡ ይኸው እግዚአብሔር፡ "ኢየሱስ መሲሕ" ተብሎ፡ በሰውነት፡ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ፡ ለሐዋርያቱ፡- "**ኢታጥርዩ ለከሙ፡ ወኢትፁሩ ኢአሣእነ!** ለእናንተ ጫማም ቢኾን፡ አይኑራችሁ! አትያዙም!" ያለውን በማዘከር፡ ከኪዳናውያንና ከኪዳናውያት መካከል፡ አንዳንዶቹ፡ ያለጫማ የሚኼዱት፡ ለካ ለዚህ ነውና!» ብሎ፡ እውነታውን ይገነዘባል። (ዘፀአ. ፫፥ ፭። ማቴ. ፲፥ ፲፤ ሉቃ. ፲፥ ፬።)

፰. ታዲያ! «እግዚአብሔር፡ ከሰው፣ ሰውም፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ አንድ የሚኾነው»፣ እንዲሁም፡ በቅድስቲቱ የትንሣኤ ሕይወትና በዘለዓለማዊቱ የሰንበት ዓለም፡ ፍጻሜ በሌለው ገነታዊና መንግሥተ-ሰማያዊ ሕይወት፡ በነፍስና በመንፈስ ብቻ ሳይኾን፣ በሥጋው አካልና ባሕርይ ጭምር፡ ከእርሱ ጋር ዐብሮ ለመኖር መቻሉን ለማረጋገጥና በማረጋገጥ አይደለም እንዴ! ፈጣሪ እግዚአብሔር ወልድ፡ኢየሱስ መሲሕ፡ እንዲህ ሲል፡ ቁርጡን የተናገረው?

ይኸውም፡- "**ዘበልዐ ሥጋየ፣ ወሰትየ ደምየ፡ ቦ ሕይወት ዘለዓለም! ወይሄሉ ምስሌየ! ወአነሂ፡ እሄሉ ምስሌሁ! አማን አማን እብለከሙ፡ እመ ኢበላእክሙ ሥጋሁ ለወልደ-ዕጓለ እምሕያው፣ ወኢሰተይክሙ ደሞ፡ አልብክሙ ሕይወት ላዕሌክሙ።** ሥጋዬን የበላ፣ ደሜንም የጠጣ፡ የዘለዓለም ሕይወት አለው! እርሱ፡ ከእኔ ጋር ይኖራል! እኔም፡ ከእርሱ ጋር እኖራለሁ! እውነት እውነት እላችኋለሁ! የማርያምን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፣ ደሙንም ካልጠጣችሁ፡ በእየራሳችሁ፡ ሕይወት አይኖራችሁም።" ያለው?» ብሎ፡ የእውነታውን፡ ሌላኛውን ገጽታ ይገነዘባል። (ዮሐ. ፮፥ ፳፮-፷፬።)

፰. "እግዚኣብሔር፡ እንዲህ፡ በባሕርይ፡ ኣንድ ሲኾን፣ በስም፣ በአካልና በግብር ግን፡ ሦስት ነው!" እንደምንል ኹሉ፡ ሰውም፡ እግዚአብሔርን ከመምሰሉ የብቅዓት ደረጃ ሲደርስ፣ ይኸውም፡ በተለይ፡ ከማሕፀን ጀምሮ፡ ነፍስ እስኪያውቅ ድረስ ባለው ዕድሜው፡ እንደፈጣሪው ኹሉ፡ በሰውነት የተፈጥሮ አቋሙ፡ በስም፣ በአካልና በግብር፡ ሦስትነት ያለው ቢኾንም፣ እንዲሁ፡ "በባሕርዩም፡ ነፍሱና ሥጋው፣ መንፈሱም፡ አንድ ኾነው የተስማሙለት ስለኾነ፡ ከፍጹሙ የዕውቀት ብቅዓት ደረሰ!" እንላለን።

ይኸውም፡ የሥጋ፥ የነፍስና የመንፈስ ፈቃዳት፡ በፍጹም ተስማምተው፣ በተለይ፡ ነፍስና ሥጋ፡ ያ ሰው፡ ገና በማሕፀን፡ በሦስተኛነት የተሠራበትንና እግዚአብሔራዊ የኾነውን፡ ያን ቅዱስ መንፈስ፡ በነጻ ፍላጎታቸው ተቀብለውት፡ ለዓቅመ-አዳም እና ለዓቅመ ሔዋን ደርሰው፡ "ነፍስ-ዐወቁ" ከተባሉበት ዕድሜ በኋላም፡ በእርሱ በሚመሩበት ጊዜ፡ በተዋሕዶ አንድ ኾነው፣ በመለኮታዊው ሥርዓት የሚኖሩ መኾናቸው ጭምር ሲረጋገጥ ማለት ነው።

እዚህ ላይ፡ ነፍስና መንፈስ፡ ገና ከጥንተ-ተፈጥሯቸው ጀምረው፡ ዐዋቂዎች ሲኾኑ፡ ሥጋ ብቻ፡ በተፈጥሮ፡ የዕድገት ሥርዓቱ፡ "ነፍስ-ዐወቀ!" ወይም፡ "ለአካለ-መጠን አደረሰ!" እስኪባል ድረስ፡ ከእነሁ፡ ከነፍስና ከመንፈስ ጋር፡ የዕውቀቱ ተካፋይ ሊኾን እንደማይችል መገንዘቡ አግባብ ይኾናል።

ከላይ የቀረበውን እውነታ ለማስረዳት፡ ከወንድ፡ ሄኖክን፣ ከሴት፡ ድንግል ማርያምን፡ በአርአያነት ማቅረብ ይቻላል። ይህም ማለት፡ ያ ሰው፡ በጥንተ-ተፈጥሮውና በንጽሓ-ጠባዩ፡ ጸንቶ ከተገኘ፡ ሴቷ፡ ድንግል ማርያምን ወንዱ ደግሞ፡ ሄኖክን መስለው፣ "ምንጊዜም፡ ሞት ሳይነካቸው፡ ለዘለዓለም፡ በሕያውነት ይኖራሉ!" ማለት ነው፤ ይኸውም፡ "በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረ! ከእኛ እንደአንዳችንም ኾነ!" የተባለው ሰው፡ ይህን የመሰለውን፡ ፈጣሪውን ያስመሰለውን ፍጹምነት፡ ይዞ ከተገኘ ማለት ነው፤ ማለትም፡ ያን፡ ካላሳደፈው፥ ወይም፡ ካላስወገደው በቀር፡ "በዚያው፡ በተፈጠረበት፡ በእግዚአብሔርነት መልኩ እና ከቅድስት ሥላሴ እንደአንዳቸው በኾነበት ማንነቱ ይቀጥላል!" ማለት ነው።

ለዚህም ተጨማሪ ምስክር፡ ከሴት፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻት ድንግል ማርያም እና ከወንድ፡ እግዚአብሔር ወልድ የተዋሓደው፡ ኢየሱስ መሲሕ ይጠቀሳሉ።

፱. ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ ሰዎች፡ ወንዶችም፣ ሴቶችም፡ በፈጣሪያቸው ታላቅ ቸርነት ከተሰጣቸው፡ ከፍጹሙ የማሰብ ነጻነታቸውና የመምረጥ መብታቸው፣ የመወሰን ሥልጣናቸውና የመፈጸም ኃይላቸው የተነሣ፡ እንደእግዚአብሔር መኾንን፥ ወይም፡ እርሱን መምሰልን፡ ለእየራሳቸው፡ በእውነትና በእርግጥ ፈልገውና መርጠው ቢኾን ኖሮ፡ ጥንቱኑም፡ በአዳም እና በሔዋን ፍላጎትና ምርጫ፡ ይህ ፍላጎታቸውና ምርጫቸው፡ ተፈጽሞ ይታይ ነበር።

ኋላ፡ ድንግል ማርያም እና ኢየሱስ መሲሕ ኾነው እንደተገኙት ማለት ነው። ነገር ግን፡ ስላልፈለጉና ስላልመረጡ ብቻ፡ እውነታው፡ ሳይኾን ቀረ።ከዚያ ወዲህና ዛሬም እኮ፡ ከፈለጉና ከመረጡ፡ እንደድንግል ማርያም እና እንደኢየሱስ መሲሕ መኾን ይቻላቸዋል። እነሆ! እየተቻላቸውም እኮ፡ ፈጽመውት የተገኙ አሉ።

ይኹን እንጂ፡ ማንኛዪቱም ሴት እና ማንኛውም ወንድ ኹሉ፡ ከአዳም እና ሔዋን አንሥቶ፡ ያን፡ እግዚአብሔርን የመሰለበትን፣ በዚያ፡ ንጽሓ ጠባይ የከበረበትንም ጥንተ-ተፈጥሮውን ካሳደፈው፣ ስላሳደፈውም፣ ካስወገደው፥ ስላስወገደውም፡ ያው፡ በአዳምና በሔዋን የተወጠነው፡ ይህን የመሰለው፡ የስሕተት ጐዳና፡ እነሆ፡ እስከዛሬ ቀጥሎ፡ ጉዳቱና ጥፋቱ ይኸው ያለማቋረጥ ሲካኼድ ይታያል።

በተቀረ፡ በጥንተ-ተፈጥሮ፡ እንዲህ በንጽሓ-ጠባይ የጠዳውና የከበረው፡ የእየአንዳንዱ ሴት፥ ወይም፡ ወንድ፡ ሥጋዊውና ነፍሳዊው፥ መንፈሳዊዉም አካልና ባሕርይ፣ በጠቅላላ ሰውነቱ፡ እንደሠሪው እንደእግዚአብሔር፡ ንጹሕ፥ ፍጹምና ቅዱስ ነው። ከዚህ ንጽሕናውና ፍጹምነቱ፣ ቅዱስነቱም ለይቶ የሚያስወጣው፡ ከላይ ተደጋግሞ እንደተነገረው፡ እያንዳንዱ ሰው፡ በእየራሱ፣ በየግሉ እንዲሠራበት፡ መለኮታዊ ጸጋው ኾኖ፡ ከፈጣሪው በተለገሠውና ስጦታው በኾነው፡ በአሳቤ መብቱና በምርጫ ነጻነቱ፣ በውሳኔ ሥልጣኑና በማድረግ ኃይሉ፡ ለክፋቱ ብቻ ሲጠቀምበት ነው።

ስለዚህ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፣ በአገልግሎቷና በአገልጋዮቿም ዘንድ ያለው የሃይማኖትና የምግባር፣ የተስፋና የብቅዓት ይዞታ፡ ይህ፡ የማሰብ ነጻነትና የምርጫ መብት፣ የመወሰን ሥልጣንና የማድረግ ኃይል፥ መለኮታዊ ጸጋ እንጂ፣ ደግሞም፡ በዚህ ጸጋ፡ በመልካም ጎኑ ተጠቅሞ፡ ራስን፡ ባላዋቂነት ማጥፋት ሳይኾን፣ በዐዋቂነት ማዳን እንጂ፡ "ጥንተ-አብሶ"፡ ማለትም፡ በዘርና በትውልድ፡ ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ ኃጢአት እንዳለ አድርጎ የሚያቀርበው ስሑት ይትበሃል አይደለም። ከዚህ የተነሣ፡ በእነዚህ ዘንድ ያለው፡ <u>ንስሓ</u> ብቻ ነው።

፲. እያንዳንዱ ሰው፡ ከፈለገና ከመረጠ፡ የቀደሙትን አዳምንና ሔዋንን ከመምሰል ይልቅ፡ ድንግል ማርያምንና ኢየሱስ መሲሕን ለመምሰል የሚቻለው መኾኑ ታውቋል፤ ታይቷል፤ ተረጋግጧልም። ይህንም እውነታ ለማሳመን፡ አኹንም፡ ራቅ ወዳለ፡ ወደሌላ ምስክር ፍለጋ መኼድ አያሻንም። በቅርቡ፡ የሊቀ-ሓዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስን፡ አንዱን ዝክረ-ነገሩን፡ እዚህ ላይ፡ ለአብነት፡ እንዲህ እያልን እንጠቅሰዋለን።

ያም፡ ዝክረ-ነገር፡- "**ወበጺሖ እግዚእ ኢየሱስ፡ ብሔረ ቂሣርያ ዘፊልጶስ፡ ተስእሎሙ ለአርዳኢሁ፡ እንዘ ይብል፡ 'መኑ ይብልዎ ሰብእ፡ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው?'**

**"ወይቤልዎ፡- 'ቦ እለ ይብሉከ፡ ‹ዮሐንስሃ መጥምቀ!› ወካልአን ይብሉከ፡ ‹ኤልያስሃ!› ወመንፈቆሙ ይብሉከ፡ ‹ኤርምያስሃ! ወእመ አኮ፡ አሓዱ፡ እምነቢያት ቀደምት!›**

**"ወይቤሎሙ፡- 'አንትሙኬ፡ መነ ትብሉኒ?'**

**"ወአውሥአ፡ ስምዖን ጴጥሮስ፤ ወይቤ፡- 'አንተ ውእቱ፡ መሲሕ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው!'**

**"ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ፤ ወይቤሎ፡- 'ብፁዕ አንተ፡ ስምዖን ወልደ-ዮና! እስመ ኢከሠተ ለከ፡ ዘሥጋ፥ ወደም፤ አላ፡ አቡየ ዘበሰማያት።'**

"ጌታችን ኢየሱስም፡ የፊልጶስ አገር ወደምትኾን፡ ወደቂሣርያ ከተማ በደረሰ ጊዜ፡ ደቀ መዛሙርቱን፡- 'ሰዎች፡ የማርያምን ልጅ [እኔን] ማን ይሉታል?' ብሎ ጠየቃቸው።

"እነርሱም፡- ‹'ዮሐንስ መጥምቅ ነህ!' የሚሉህ አሉ፤ ሌሎችም፡ 'ኤልያስ ነው!' ይሉሃል፤ እኩሌቶቹም፡ 'ኤርምያስ ነው!' ይሉሃል፤ ያም ባይኾን፡ 'ከቀደሙት ነቢያት፡ አንዱ ነው!' ይሉሃል፤› አሉት።

**"እርሱም፡- 'እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ?' አላቸው።**

"ስምዖን ጴጥሮስም፡ መልሶ፡- **'አንተ፡ መሲሕ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!'** አለው።

"ጌታችን ኢየሱስም መለሰ፤ አለውም፡- 'አንተ! የዮና-ልጅ ስምዖን፣ ብፁዕ ነህ! **ይህን እውነት የገለጸልህ፡ የሥጋና የደም ዕውቀትህ አይደለም፤ የሰማዩ አባቴ እንጂ።"** የሚለው ነው። ማቴ. ፲፮፥ ፲፫-፲፯።)

አዎን! መምህራችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡- "ይህን እግዚአብሔራዊ እውነት የገለጸልህ፡ 'የሰማዩ አባቴ ነው!'" ብሎ፡ ለማንኛውም ሰብኣዊ ፍጡር እንደሚያደርገው፡ ምስጢሩን በማውጣት፡ ለቅዱስ ጴጥሮስም የነገረው፡ ያ፡ 'የሰማዩ አባቴ!' ያለው፡ ማንን ይመስለናል?

**የቅዱስ ጴጥሮስን መንፈስ እኮ ነው!** አዎን! በእርሱው፡ በሓዋርያው፡ በቅዱስ ጴጥሮስ ዘንድ፡ ከማሕፀን ጀምሮ፡ ከነፍሱና ከሥጋው ጋራ፡ በተፈጥሮው ዐብሮት የተሰጠውን፡ ያንኑ፡ ሦስተኛውን፡ **የራሱ መንፈስ የኾነውን፡ የተፈጥሮ አካሉንና ባሕርዩን እኮ ነው!** መለኮታዊ መምህሩ፡ "የሰማዩ አባቴ" ያለው።

እግዚአብሔር ወልድ፡ ሕፃን ስምዖንን፡ ገና በማሕፀን ሲፀነስ፡ በቅድሚያ፡ በሥጋው ካበጀው በኋላ፡ እግዚአብሔር አብወእም፡ መልካቸው የኾነችውን ነፍሳቸውን፡ "እፍ!" ብለውባት፣ ከዚያ ቀጥሎ፡ ከሥላሴ፡ እንደአንዳቸው ለመኾን ካበቃችው፡ ከዚያች፡ "ከፉና ደጉን ለይታ ከምታስታውቀው፡ ከመንፈስ-ቅዱስ የዕውቀት ዛፍ ፍሬ፡ ወዲያው ሲበላ፣ በዚያች ቅጽበት ያገኘውን፡ ያንን መንፈሱን እኮ ነው፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ "የሰማዩ አባቴ" ያለው።

በዚያን ጊዜ፡ **ያ፡ የሐዋርያው ጴጥሮስ መንፈስ፡** በመምህሩ መለኮታዊ ነደ-እሳት ቃለ-መጠይቅ ሲፈተን፡ በሃይማኖቱ ብቅዓት፡ ከንጽሕናውና ከፍጹምነቱ፣ ከቅድስናውም ደረጃ ለመድረሱ፡ በራሱ መልስ፣ ከፈጣሪውም በተቀበለው የምስክርነት ሙገሳና ክብር ተረጋግጧል።

ደግሞም፡- **"ወሶበ ያገብኡክሙ፡ ኢተኀልዩ ዘትነብቡ፤ ወዘትትናገሩ፤ እስመ ይትወሀበክሙ በይእቲ ሰዓት፡ ዘትትናገሩ። እስመ ኢኮንክሙ አንትሙ፡ ዘትነብቡ፤ አላ፡ መንፈሱ ለአቡክሙ ሰማያዊ፤ ውእቱ ይትናገር በላዕሌክሙ።** አሳልፈው በሚሰጧችሁም ጊዜ፡ ስለምትናገሩት፥ ስለምትመልሱትም ቃል፡ በነፍሳችሁ፡ አታስቡ! አትጨነቁ! በዚያች ሰዓት፡ ነፍሳችሁ፡ በሥጋዋ አንደበት የምትመልሰው፡ ይሰጣታልና። የምትናገሩ፡ እናንተ አይደላችሁምና፤ የሚናገረው፡ በእናንተ ያለው፡ እርሱ፡ የሰማዩ አባቴ መንፈስ ነው እንጂ።" የሚለው አለ።

የዚህም፡ የኹለተኛው ጥቅስ፡ የትርጓሜ ሓተታ፡ ከቀደመው፣ ከላይኛው፡ የተለየ አይደለም፤ ያው፡ አንድ ነው። አዎን! በእያንዳንዳችን ዘንድ፡ ከማሕፀን ጀምሮ፡ ከነፍሳችንና ከሥጋችን ጋራ፡ በተፈጥሮአችን ተሰጥቶን፡ ዐብሮን ያለውን፡ ያንኑ፡ ሦስተኛውን፡ **የየራሳችን __መንፈስ__ የኾነውን፡ የተፈጥሮ አካልና ባሕርይ እኮ ነው!** መለኮታዊ መምህራችን፡- "የሚናገረው፡ **በእናንተ ያለው፡ እርሱ፡ __የሰማዩ አባቴ መንፈስ__ ነው እንጂ!"** ያለው። እውነተኛው መምህራችን ኢየሱስ መሲሕ፡ "**የሰማዩ አባቴ __መንፈስ__**" ያለው፡ አዎን! **__ያንን መንፈሳችንን__** ነው። (ማቴ. ፲፥ ፲፱-፳።)

ሓተታዬን ከመዝጋቴ በፊት፡ ባለፉት ብቻ ሳይኾን፡ በዚህኛውም የምርምር ድርሰትህ፡ በሥነ-ጽሕፈትህና በሥነ-ቃላትህ፥ በሥነ-አሌፋትህና [ብዙ ያላተኰርሁበት ብኾንም እንኳ]፡ በሥነ-ነቍጣትህ ጭምር ረገድ፥ ባደረግኸው ጥንቃቄ፡ ከመደሰቴ የተነሣ፡ ምግባርህን ሳላደንቅና ሳልመርቅህ አላልፍም።

በዚህኛው የምርምር ጽሑፍ ውስጥ፡ በምንባብ ጊዜ፡ እግረ-መንገዴን ያገኘኋቸውን፣ በኹላችንም ዘንድ የተለመዱ የፊደላት ግድፈቶችን፡ በቀይ ቀልሜአቸዋለሁና፡ ካየሃቸው በኋላ፣ የምታጠቍራቸው ናቸው።

ይህ፡ የደብዳቤ ልውውጣችን፡ እንዳለፉት ጊዜያት ኹሉ፡ አኹንም፡ ለአንባቢዎቻችን ትምህርትና የዕውቀት ደረጃቸውን በበለጠ ለማሳደግ እንዲረዳቸው፡ የክህነት ባልደረቦቻችን፡ ይህንኑ ጽሑፍህን፡ በጎዋ-ሰሌዳችንና በፌስ-ቡክ፥ በሌሎቹም፡ የጎዋ መድረኮቻችን ላይ፡ ከእኔ መልስ ጋር ዐብረው በማውጣት፡ ለይፋ ምንባብ ያበቁት ዘንድ፡ የዚህን ጽሑፍ ቅጂ ጭምር፡ ለእነርሱም አስተላልፌላቸዋለሁና፡ አንተም፣ እነርሱም፡ የሚጠቍረውን አጥቍራችሁ፡ የቀረውንም ጽሑፍ፡ ለተባለው አገልግሎት ታውሉት ዘንድ፡ ይኸው፡ በልሙጡ የአብነት እና የነባር ሰነድ ቅጽነቱ፣ በኹለቱም መልኩ ከውኜ፡ ለኹላችሁም ልኬላችኋለሁ።

በቅዱሱ ኪዳን ወንድምህና የአገልግሎት ባልደረባህ፦
ኪዳናዊ ኤርምያስ [ንቡረ-እድ ዘአኵስም ጽዮን]